አዘጋጅ
ዳምጤ አሰማኸኝ

ሞዓ አንበሳ

የሐምሌ እትም   የፖስታ ሣጥን ቁጥር 9056   አርሊንግተን ቬርጂኒያ 22204   ስልክ ቁጥር (703) 998 5152   ዋጋ $1.00

ርዕሰ አንቀጽ

ኢትዮጵያ አሁን ካለችበት እጅግ እስከፊና አስጊ የሽግግር ጊዜ ውስጥ ያለን አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን በሙሉ፣ ከጥንት ጀምሮ ሲወርድና ሲያያዝ የመጣውን የአባቶቻችንን ባህልና ቅርስ እንደ ነበረና እንደ ተጠበቀ አድርጐ ለማቆየትና ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፍ ለማድረግ ባለን ከፍተኛ ምኞት ተነሣሥተን "ሞዓ አንበሳ" ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል ተብሎ የተሠየመውን በአሜሪካን የስደት አገራችን ውስጥ አቋቋምን።

የድርጅቱ ዋና ዓላማ ኢትዮጵያ ባላት ባህል፣ ወግና ሥርዓት መሠረት፣ ያገሪቱን ነፃነት የሕዝቡን አንድነት፣ የዕኩልነት መብታችንም ተጠብቆ የኖረው በዘውዱ የበላይ ሰብሳቢነት መሆኑን ከታሪክ አግኝተን ነው። ሕዝቡ ከባህሉ፣ ከልማዱና ከሃይማኖቱ ጋር ዘውዱ የተሣሠረ በመሆኑ፣ ጥንታዊ ታሪኩን ሳይለቅ መራመድ ምርጫው መሆኑንም አረጋግጠን ነው። በዚሁ መሠረትበአሁኑ ወቅት የሞዓ አንበሳ አርበኞች በጠቅላላው ኢትዮጵያ ከወያኔው ጋር ተጋጥመው ሲያርበተብቱት "አትነሣም ወይ! አትነሣም ወይ!የሞዓ አንበሳ አይደለህም ወይ! እያሉ ወያኔውን መድረሻ አሳጥተውት ስናይ፣ ደስታችን ከመጠን በላይ በመሆኑ ነው።" ይኸንን ሕዝባዊና ብሔራዊ አርበኝነት ለመሳተፍ የኢትዮጵያንም ነፃነት ፍፃሜ ለማድረስ የመንፈስ ግለታችን እየናረ ወያኔውንም በማጣደፍ ላይ ስለሚገኝ ነው።

ዘውድ የሕዝብ ነው። አገር የምትረጋውና የሕዝብ ሰላም የሚሠፍነው በዘውድ ሲሆን፣ ለአምስት ሺህ ዘመናት ፀንቶና የኢትዮጵያ ነፃነት ተጠብቆ ሊኖረ የቻለው በዘውዱ ጠንካራነት ነው። ከኢትዮጵያ የዘውድ ታሪክ ውስጥ፣ ዘውድ የተዳከመበትና ከቦታ ቦታ የተሰደደበትም ወቅት ነበር ዘመነ መሳፍንት አንዱ ተጠቃሽ ማስረጃ ሲሆን፣ የኢጣሊያን ፋሽስት ወረራና የኮሚዩኒስቶችም የእጅ አዙር (ግራ) ወረራ ተደጋጋሚ ማስረጃ ሆኖ ሊቀርብ በመቻሉ ነው። በዚህም የደርግ ዘመን በየጠቅላይ ግዛቱ ደርግን ሲያርበደብድ የተዋደቀው አርበኛ ታሪኩን ጨብጦ በመገኘቱ ነው።

የሕዝቡና ያገሪቱ ልዩ መታወቂያ የሆነው ዘውድ፣ ለተመልካቾች የጌጥ፣ የመከበሪያ፣ የመመኪያና የአንድነት ዓምድ ሆኖ በመገኘቱ ነው። ዘውድ የሕዝቡ መሠረት፣ የሕዝቡ ዋልታና የታሪኩ ጋሻ ነው። ስለዚህም ሒደቱ እንዲቀጥል ታሪኩን የተረከበው ያሁኑ ትውልድ "ሞዓ አንበሳን" በአስተባባሪ አካልነት አቋቁሞ የኢትዮጵያን ነፃነት ለማወጅ "የክተት ጥሪ" ሲያቀርብ፣ በደም ፍላት የሚሽቀዳደመው ኢትዮጵያዊ ተስፋ የተሞላው መሆኑን ለመግለጽ የዓለምን ሕዝብ ምስክር አድርጐ ክብርና ኩራቱን ለታሪክ ሲያስተላልፍ በመገኘቱ ነው።

የሞዓ አንበሳ ጀግና

በሁለተኛው የዓለም ጦርነት የኢጣሊያን ፋሺስት ኢትዮጵያን ከመውረሩዋ በፊት ከአዲስ አበባው ባቡር ጣቢያ ፊት ለፊት የቆመ የሞዓ አንበሳ ሐውልት ነበር። ፋሺስት ኢጣሊያን ይኸንን የሞዓ አንበሳ ሐውልት ነቅላ ወደ ሮም ከተማ ወሰደችው። መሣለቂያም ለማድረግ ፋሺስቶች በከተማው አደባባይ በሞዓ አንበሳ ላይ ሲተፉበትና ሲሳለቁበት አንድ ጀግና ኢትዮጵያዊ ከሩቅ አየ። መሰናዳት ጀመረ። የአባቶቹን ጐራዴ አነገተ። በሞዓ አንበሳ ላይ ወደሚሳለቁበት ሥፍራ ገሠገሠ። ደሙ ፈልቶ ራሱን አያውቅም። በዚያን ጊዜ ያስታውስ የነበረው የናት አገሩንና የሞዓ አንበሳን ውርደት ብቻ ነበር። ጐራዴው ተመዟል። ወደ ሐፎቱ አይመለስም። ፋሺስቶቹን እያሩዋሩዋጠ ሲጨፈጭፍ ታየ። ዓለምን ናቀ። የእናት አገሩን ክብር ብቻ ተመለከተ። የኢትዮጵያም ሞዓ አንበሳ ለብዙ ሰዓቶች ብቻውን ባለበት አርፎና ቆሞ በሮም አደባባይ ላይ ታየ። ጀግናው ከዚህ የበለጠ ደስታ አልፈለገም። የሚጠብቀው ሞቱን ብቻ ነበር። ስሙ "ዘርዓይ ደረስ" ይባላል። ኢትዮጵያዊ ሁሉ የዘርዓይ ደረስን የጀግንነት ታሪክ ባስታወሰ ቁጥር ለሞዓ አንበሳ መታገልን ከነፃነቱ ጋር ያዋህደዋል።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት አፄ አምኃ ሥላሴ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው ሊገቡ የነበራቸው ደስታ በዚህ መልክ ሲሆን የልዩ ጽ/ቤት ሹማቸውም አብሮ ይታያል።

የታሪክ እንቅፋት

ለማስረዳት ያህል ግርማዊ ቀዳማዊ አምኃ ሥላሴ ቀደም ሲል ለወገናቸው ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያወጡትን መግለጫ እናቀርባለን። የረጅም ዘመን አኩሪ ታሪክ ባለቤት የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ በየዘመኑ ባደረገው ከፍተኛ ተጋድሎና በከፈለውም መስዋዕት የአገራችን አንድነትና ህልውና ተጠብቆ ቆይቷል። የዛሬውም ተተኪ ትውልድ ይህን ጀግኖች አባቶች ደማቸውን አፍስሰው አጥንታቸውን ከስክሰው ያቆዩለትን ቅርስ የመጠበቅ ግዴታ አለበት።

በአሁኑ ወቅት ሕዝባችን ታሪካዊ አንድነቱን በይበልጥ ለማረጋገጥ የሚያደርገው ጥረት የሚያበረታታ ነው። የአገራችንን አንድነትና ነፃነት ማስከበር፣ ሕዝቡም መብቱ በእኩልነት እንዲጠበቅ ፍትሕና ርትዕ እንዲያገኝ ማድረግ ሕዝቡ የጣለብን አደራና ከታሪክም የወረስነው ከፍተኛ ሃላፊነት ስለሆነ ይህንኑ ሃላፊነት ለመወጣት ቆርጠን ተነስተናል። ለዚሁም ኃያሉ እግዚአብሔር ይርዳን። ምክር ቤቱ ጉዞውንም በሚመለከት ባቀረበው ቃለ ጉባኤ መሠረት ንጉሠ ነገሥቱ የሚያዙበት ጠቅላላ ገንዘብ በእቴጌይቱ እጅ ሆኖ ሥራውን ለማራመድ በደረሰው ጥፋት በጥንቃቄ አስበውበት ንጉሠ ነገሥቱ የካቲት 16 ቀን 1985 ዓም የጻፉትን ትዕዛዝና ሌላውንም በዝርዝር ተከታታይ አድርገን እናቀርባለን።

እቴጌይቱ በስዊስ ባንክ የሚገኘውንና ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የተወረሰውን ሀብት ብቻ ሳይሆን፣ በአሁኑ ጊዜ ከእንግሊዝ ንጉሣዊ ዙፋን፣ ከስዊድን፣ ከኖርዌይ፣ ከቤልጂግ፣ ከጃፓን፣ ከሣውዲ፣ ከሞሮኮ፣ በጠቅላላው ከሌሎቹም የዘውድ መንግሥታት እንዲሁም ከአሜሪካን መንግሥት ሳይቀር፣ ከሀብታም ኩባንያዎች ከጀማይካና ከዕሥራኤልም ሁሉ፣ በየወሩ ከመጠን በላይ የገቢ ምንጭ ገንብተው፣ ይፈነጩበታል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን ፊት በደርግ በኋላም በወያኔ ጦርነት እየተቀጠቀጠ፣ በረኃብ አለንጋ ይገረፋል። አፄ አምኃ ሥላሴ የንግሥቲቱን የግፍ ሥራ እተኩረው ከተመለከቱ በኋላ፣ እጅግ አምርረው የጻፉላቸውን ደብዳቤ ስንመለከት ራሱ ቋሚ ምስክር ሆኖ ሁለቱንም ጐን ለጐን አቁሞ ለታሪክ ያስተላልፋቸዋል።

ከዚህም በስተቀር ንጉሡ የሕዝቡን ጥሪ አክብረው በሕዝባቸው መካከል ለመገኘት ቢዘጋጁ ንግሥቲቱ ገንዘባቸውን ከለከሏቸው። ከስቴት ዲፓርትሜንት የመጓጓዣ ገንዘብ ቢጠይቁ፣ ለብዙ ዓመታት የሚበቃ ብዙ ሚሊዮን ዶላር ስላላቸው፣ ዕርዳታ አያስፈልጋቸውም፣ በፖለቲካ በኩል ግን ዕርዳታችንን አናስተጓጉልም። ከዚሁም ጋር ወደ አገራችሁ በምትገቡበት ጊዜ፣ ድጋፋችን

ወደ ገጽ..2. ይዞራል

የገጽ ማውጫ

ቁጥር
1. ርዕስ አንቀጽ .... ፩
2. የሞዓ አንበሳ ጀግና...... ፩
3. የታሪክ እንቅፋት .... ፩
4. ትምህርት የመግደል ዘመቻ. ፫
5. አጭር የኢህአፓ ታሪክ .... ፫
6. ኮሚዩኒዝም ቀዘቀዘ፣ ረከሰ፣ ተተፋ .... ፬
7. ከደርግና ከወያኔ ጋር የተደረጉ ጦርነቶች...... ፯

ከገጽ ...1... የዞረ

አይለያቸሁም አሏቸው። ይኸንን ሁሉ ለማከናወን፣ የተቸገሩበትንና ለእቴጌይቱ የጻፉትን እንመልከት

የካት 16 ቀን 1985 ዓም

ለተወዳጅዋ እቴጌ መድፈሪያሽ ወርቅ

የካቲት 4 ቀን 1985 ዓም ከምክር ቤታችንና ከሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል ኃላፊዎቻችን የቀረበልንን ማስታወሻ ተመልክተን ከዚህ ቀደም የፈቀድነው ለባጀት እስካሁን ወጭ ሆኖ ባለመከፈሉ ሥራው ከፍተኛ በደል የደረሰበት በመሆኑ በቃልም ቀርበው በዝርዝር በማስታወስ ችግሩ እንዲቃለል ባለመደረጉ የሚከተለውን ትዕዛዝ ጥተናል።

ካሁን በፊት ለሕዝባችን በገባነው ቃል መሠረት ከእንግዲህ ወዲያ ወደፊት እንጂ ወደኋላ ማለት አይቻልም።

ስለዚህ የተደከመበትና የተሰራው ሁሉ መና ሆኖ እንዳይቀር በታሪክም ተወቃሽነት እንዳያስከትል ደጋግመን ገንዘብ አለን ሥራው ይቀጥል ብለን ባዘዝነው መሠረት የተፈቀደው ባጀት ወጭ ሆኖ እንዲሰጥ አዘናል።

1ኛ. በአዲስ አበባ ለሚካሄደው የሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አካል ማዕከላዊ ጽ/ቤት ደሞዝና ሥራ ማስኬጃ በወር የኢት. ብር 25,000.00 በሞዓ አንበሳ ሊቀ መንበር አማካይነት በአስቸኳይ ወጭ ሆኖ እንዲላክ ይሁን

2ኛ. ለሕገ መንግሥት አርቃቂ ኮሚቴ ተብሎ ለተቋቋመው የሞዓ አንበሳ ዙፋነዊ አሰባሳቢ አካል ወኪሎች ባቀረቡት መሠረት አስፈላጊው የሥራ ማስኬጃ ወጭ ሆኖ እንዲላክላቸው

3ኛ. በአክተን የሚገኘው ልዩ ጽ/ቤታችን የሥራ ማስኬጃና የሠራተኞች ደሞዝ እስካሁን ካልተከፈላቸው ጊዜ ታስቦ በአስቸኳይ ወጭ ሆኖ እንዲከፈላቸው።

4ኛ. ስለ አዲስ አበባ ጉዞአችን ጉዳይ ባጀቱ ተጠንቶ በቀረበው መሠረት አስፈላጊው ሁሉ እንዲጠናቀቅና ባጀቱ ወጭ ሆኖ እንዲሰጥ እንዲሁም የጉዞአችን ጉዳይ እንዲፋጠን ወስነናል።

ቀዳማዊ አጼ አምኃ ሥላሴ
ንጉሠ ነገሥት

ከዚያም አልፈው ንግሥቲቱ የንጉሠ ነገሥቱን ትዕዛዝና መመሪያ በመጣስ ልዕልት ማርያም ሥናን የኮሚቴ ሰብሳቢ አድርገው ሾሙ። ልዕልት ማርያም ሥና ከዚህ በፊት ንጉሠ ነገሥቱ ሾመዋቸው የነበረውን የዘውድ ምክር ቤት ሰብሳቢነት አልፈልግም ብለው የሄዱ መሆናቸው ይታወሳል።

የንጉሠ ነገሥቱ የዘውድ ምክር ቤት በዚሁ የስደት አገር ወስጥ በተሰጠው መመሪያ መሠረት ተረክቦ ሥራውን ለመሥራት ሲዘጋጅ ንግሥቲቱ የንጉሡን ውሳኔ በማስተባበል፣ የምክር ቤቱ ሥራ እንዲጓደል አድርገውታል። ኃላፊዎቹም እንዲበታተኑና ንጉሡ የሰጡትንም ማዕርግ እስከ መግፈፍ ሞክረዋል። በንጉሠ ነገሥቱ ስም እየተጠቀሙ፣ ከሕግ ውጪ በሆነ አሠራር የዘውድ ምክር ቤቱ ሳይመከርበትና ሳያውቀው ሕገ ወጥ ውሳኔ በማስተላለፍ ወንጀል ፈጽመዋል።

ይኸንኑ ደባቸውን ተገንዝቦ የዙፋን ምክር ቤት በግንቦት 27 ቀገ 1993 የሚከተለውን ውሳኔ አስተላልፏል።

May 27, 1993

የግርማዊነታቸው የምክር ቤቱ ቃለ ጉባኤ
==============================

ጀኔራል ዓባይ የማኑ የግርማዊነታቸው ልዩ ጽ/ቤት ሹምና የበላይ ዋና ተጠሪና ኃላፊ በአጀንዳ መልክ ባቀረቡት መሠረት ከዚህ ቀደም ተደጋግሞ በግርማዊ ጃንሆይ የተሰጠውን መመሪያና ትእዛዝ በመጣስ ግርማዊት እቴጌ በሥራው ጣልቃ እየገቡ እንቅፋት በመሆን በሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል አሠራር ላይ ደባ ስለፈጠሩ ቋሚ ትእዛዝ ከግርማዋነታቸው እንዲሰጥ በማለት በቀረበው ሃሳብ ላይ ምክር ቤቱ ከተወያየበት በኋላ ከሚከተለው ውሳኔ ደርሷል።

ሥራው በግርማዊነታቸው ማዕከላዊነት ቅደም ተከተሉን ይዞ እንዲሠራ እንጂ ማናቸውም ጉዳይ በጎን እንዳይደረግ ተብሎ ከዚህ ቀደም ከግርማዊነታቸው ታዟል። ይሁን እንጂ ግርማዊነታቸውን ለማሳሳትና ሥራውን ለማደናቀፍ በጎን የሚደረገው መራወጥ አሁንም አለማቋረጡን ምክር ቤቱ ደርሶበታል። ስለዚህ የቀድሞውን ትዕዛዝ በማጠናከር ሥራውን የሚያዳክም ማንኛውንም እንቅፋት የሚያስወግድ የማያሻማ ግልጥ ትእዛዝ በድጋሚ እንዲሰጥበት ምክር ቤቱ ለመጨረሻ ውሳኔ ለግርማዊነታቸው እንዲቀርብ ተስማምቷል።

የኢትዮጵያ አልጋ ወራሽ ከባለቤታቸው ከልዕልት ኑኑ ጌታሁንና ከልጃቸው ከልዕልዕት ልደታ ዘርዓ ያዕቆብ ጋር

ንጉሠ ነገሥቱም ውሳኔውን ተቀብለው ለንግሥቲቱ ግንቦት 29 ቀን 1993 የጻፉት ከንጉሠ ነገሥቱ ውሳኔ ጋር ተያይዞ ይገኛል።

May 29, 1993

ለተወዳጂ ኤቴጌ መድፈሪያሽ ወርቅ

ምክር ቤቱ በስበሰባ ቃለ ጉባኤ ጀኔራል ዓባይ የማኑ የልዩ ጽ/ቤታችን ሹምና የበላይ ተጠሪና ኃላፊ ለምክር ቤቱ ባቀረበው አጀንዳ መሠረት ከዚህ ቀደም በምክር ቤቱ እንዲሰራበት የሰጠነውን መመሪያና ትእዛዝ በመጣስ ግርማዊት እቴጌ በሥራው ጣልቃ እየገቡ እንቅፋት በመሆን፤ በሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል፤ አመራር

ላይ ደባ ፈጽመዋል በማለት ለምክር ቤቱ ቀርቦ ምክር ቤቱ በስብሰባ ቃለ ጉባኤ የተስማማበትና የሥራው ማዕከላዊነት ቅደም ተከተሉን ይዞ እንዲሰራና ማናቸውም ጉዳይ በጎን ምክር ቤቱ ሳያውቀው በስማችን አንድም ነገር እንዳይሰራ። ከዚህ በፊት ባዘዝነው ትእዛዝ ሊሰራ አለመቻሉንና እኛን ለማሣሣት፤ ስራውን ለማደናቀፍ፤ በጎን የሚደረገው መሯሯጥ አሁንም አለመቋረጡን ምክር ቤቱ የደረሰበት መሆኑን ምክር ቤቱ ቀርቦ በዝርዝር አስረድተዋል። ስለዚህ ከዚህ በፊት ለምክር ቤታችን በሰጠነው ስልጣንና ሃላፊነት፤ መመሪያ ማናቸውም በስማችን የሚሰራውን ሁሉ ምክር ቤታችን ሣያውቀውና ሳይመከርበት አንድም ነገር እንዳይሠራ በድጋሚ ትእዛዝ አስተላልፈናል።

ከዚህ ውጭ የሚሰራ ሁሉ ሕጋዊነትና አግባብ የሌለው መሆኑን ለምክር ቤቱ እናስታውቃለን። እቴጌዋ በሥራዋና በሞዓ አንበሳ አመራር ላይ በየጊዜው እንቅፋትና ደባ እየፈጸሙ ናቸው ተብሎ በልዩ ጽ/ቤታችን ሹምና በምክር ቤታችን የቀረበልንን ተመልክተን ለመጨረሻ ጊዜ ከዚህ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል። እቴጌዋ ከዛሬ ጀምሮ በስማችን በምንሰራው ሥራና በሞዓ አንበሳም ሆነ በምክር ቤቱ አመራር ውስጥ ጣልቃ እንዳትገባ እስከወዳኛው ጊዜ ድረስ አግደናታል።

ቀዳማዊ አጼ አምኃ ሥላሴ
ንጉሠ ነገሥት

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ወደ ኢትዮጵያ የሚመለሱበትን ምክንያት በማድረግ ከጃፓን ልዑካን ጋር በስብሰባ ሲወያዩ።

ይኸንን ሁሉ ትእዛዝ ተላልፈው ሐምሌ 8 ቀን 1985 ዓም በንጉሠ ነገሥቱ የተሰጠውን የሞዓ አንበሳ መግለጫ በማስተባበል በዘውድ ምክር ቤቱ የተሾሙትን ልዑላንና ልዕልታት እንዳልተሾሙ አድርገው በገዛ ሥልጣናቸው ንጉሡን ያለሥልጣን አስቀርተዋቸዋል።

በንጉሠ ነገሥቱ ፈቃድ የተሾሙ ለመሆናቸው ከዚህ ጋር የተያያዘው የንጉሠ ነገሥቱ ትእዛዝ ያስረዳል።

ሐምሌ 8 ቀን 1985 ዓም

የኢትዮጵያ አንድነትና ሉአላዊነት እንዲከበር፣ የሕዝቡም ደህንነት እንዲጠበቅ፣ በጠቅላላው ለአገር እድገትና ብልጽግና የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት አልጋ ወራሽ በመሆን ከተቀባንበት ጊዜ ጀምሮ ከገናናው አባታችን ከግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጐን ቆመን አገራችንና ሕዝባችንን አገልግለናል። አሁንም ጥረታችንና ፍላጐታችን ሁሉ የተጀመረውን ከግቡ ለማድረስ ነው። የኢትዮጲያ ሕዝብ ሕይወት ሕይወታችን፣ ደስታው ደስታችን

ችግሩ ችግራችን ሞቱ ሞታችን ነው። ከሕዝባችን የተለየ የግል ኑሮ የለንም፤ እንዲኖረንም አንፈልግም። የምንፈልገው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰላም አግኝቶ የተደላደለ ሕይወት እንዲኖረው ነው።

በታወቀው ምክንያት በሕዝባችን መካከል ባንገኝም በሐሳባችንና በመንፈሳችን ተለይተነው አናውቅም። በስደት ሆነን መከራውንም ችግሩንም ተካፍለናል።

አሁንም በሕዝባችን መካከል በመኖር ችግሩንና ደስታውን ለመካፈል እንዲሁም መንፈሱን ለማበረታታትና ሞራሉን ከፍ ለማድረግ ሐይሉን አሰባስቦ ታሪካዊ አንድነቱን በማደስ አገሩን በጋራ እንዲገነባ ሁሉን ለማድረግ ቆርጠን ተነስተናል። ፍላጐታችን እግዚአብሔር እስከ ፈቀደልን ድረስ የተቻለንን ሰርተን ለተተኪው ትውልድ ፅኑ መሰረት በመጣል ታሪካዊ ቅርሳችንን አስረክበን የመሸጋገሪያውን ድልድይ ዘርግተን ለማለፍ ነው።

ይህ የቆምንለትን ብሔራዊ አላማ በትክክል ግቡን እንዲመታ ለማድረግ ንጉሣወያን ቤተሰብና

ወደ ገጽ..3.. ይዞራል

ከገጽ ...2.. የዞረ

እንዲሁም አገር አፍቃሪ ለሕዝብ ተቆርቋሪ የሆኑ ግለሰቦች በሥራው እንዲሳተፉ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል።

ስለዚህ ከዚህ በታች ስማቸው የተመለከተውን፤

1ኛ. ልዑል በከሬ ፍቅረ ሥላሴ - እንደራሴ

2ኛ. ልዑል በዕደማርያም መኮንን - የአገር ውስጥ ጉዳይ መምሪያ ኃላፊ

3ኛ. ልዑል ኤርሚያስ ሣህለ ሥላሴ - የዘውድ ምክር ቤት ሰብሳቢ

4ኛ. ልጅ ዮሐንስ መንገሻ - የውጭ ጉዳይ መምሪያ ኃላፊ

5ኛ.ዶክተር አስፋ ወሰን አሥራተ - የሕገ መንግሥት መምሪያ ኃላፊ

6ኛ.ልዕልት ሥፍራሽ እምኃ ሥላሴ - የቀ.ኃ.ሥላሴ ፋውንዴሽን ቦርድ ሊቀ መንበር

7ኛ.ልዕልት ምህረት ፍቅረ ሥላሴ - የቀ.ኃ.ሥላሴ ፋውንዴሽን የሥራ አስኪያጅና

ፕሬዚዳንት በመሆን ተመድበው በመመሪያችን መሠረት እንዲያገለግሉ ወስነናል።

ቀደማዊ እምኃ ሥላሴ
ንጉሠ ነገሥት

እንዲሁም በልዩ ጽሕፈት ቤት ሹም ላይ ለአዲስ አበባ ጋዜጣ እስተላልፈው እንዲታተም ያደረጉት ትልቁ ስሕተት አይዘነጋም። በተጻፈውም ሐተታ ውስጥ "ፀሐፊው እምነት በማጉደል፣ ያልተፈቀደ ዜና በማሠራጨት ከሥራ ታግደዋል" ሲሉ እንዲታተም ያደረጉት ሁሉ ከእውነት የራቀ ነበር። ከዚሁም ጋር በንጉሠ ነገሥቱ ስም እየተጠቀሙ ንግሥቲቱ "እኛ የወያኔውን የሽግግር መንግሥት ቻርተር ተከትለን ስለምንሠራ ጄኔራል ዓባይ የግኑ ወደ ጂቡቲ የተጓዘው በንጉሠ ነገሥቱ ስም ጦርነት ለማንሣት ነውና እኛን አይወክለ'ንም"። "አንዲት ነገር ፈፅሞ ቢገኝ ኃላፊነቱ እንዳይመለከተን" ሲሉ ያስተላለፉት ደብዳቤ በማስረጃነት ይቀርባል። ይህ ሁሉ ንግሥቲቱ የኢትዮጵያን ሕዝብ ነፃነትና የአምስት ሺህ ዘመን የዙፋን ታሪክ ለማፍረስ ያቀዱ መሆናቸውን ከማረጋገጡም በላይ፣ ንጉሡ ከአባታቸው ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የወረሱትን ገንዘብ በረሳቸው ስም አዛውረው በኢትዮጵያ ሕዝብ ደም በመነገድ ላይ ይገኛሉ።

ጠቅላላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በአሁኑ ወቅት በያገሩ ክንዱን እንሥቶ በወያኔው የኮሚዩኒስት አክራሪ ላይ ጦርነት በማፋፋም ላይ በሚገኝበት በአሁኑ ስዓት ንግሥቲቱ አገራችንን ለከፍተኛ ጉዳት ሲዳርጓት ኢትዮጵያዊ ወኔያችን ያባቶቻችንን ጐራዴ ከተሰቀለበት ቆጥ አውርደን እንድንጠቀምበት ሞዓ አንበሳን ይዘህ ተጋደል። አገርህንም ለነፃነት አብቃት።

ይቀጥላል........

የአሜሪካን መንግስት ሪፓብሊካን መሪ ሴናተር ቦብ ዶል ለንጉሡ ነገሥቱ ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለሱ የመንግስታቸው እርዳታ እንደማይጓደል ሲገልጹላቸው።

ትምህርትን የመግደል ዘመቻ

የኢ.ህ.አ.ፓ አክራሪ ኮሚዩኒስት ፓርቲ የትምህርት ሚኒስትር የሆነችው "ገነት ዘውዴ" የኢትዮጵያውያን የወደፊት ትምህርት እስከ አሥረኛ ክፍል ደርሶ እንዲቆምና ከአሥረኛ ክፍል በላይ ገንዘብ እንዲከፈልበት የመንግሥቷ ተወካይ ሆና አዋጁን አስተላልፋለች።

አክራሪው የወያኔ ኮሚዩኒስት ፓርቲ የተጠቀሰውን የትምህርት ክፍያ በማጧጧፍ ባለፈው ሰኔ 6 ቀን 1994 በኮሚዩኒስት ፅንሰ ሐሳብ የተሠረፀውን መግለጫ በአማርኛ ሬዲዮ ሲዘረዝር ሰማን። መግለጫውም እንደሚያስረዳው የጥንት ነገሥታትን በመውቀስ "የግል ንብረትን" በመውቀስ ትምህርት ለሕዝቡ ሊዳረስ ያልቻለበትን ምክንያት ሊዘረዝር ሞክሯል። በሕግ ይያዙ የነበሩ ንብረቶች ምን ያህል አገሪቱን ለነፃነት እንደ ጠቀሙ ሊገልፅ አልፈለገም። ታላቁ አፄ ምኒልክ በጦር ሜዳ ለሚዋደቀው ኢትዮጵያዊ ርስት በመስጠት ብቻ እንዲጠቀም አድርገው የኢትዮጵያን ነፃነት እስከ ዛሬ አቆይተውታል።

የግል ንብረት እንዳይኖር የወያኔው አክራሪ ኮሚዩኒስት ፓርቲ የሰጠው መግለጫ የሕዝቡን የከተማ ቤትና ቦታ ቀምቶ ራሱ በገንዘቡ ሊጠቀምበት ከማቀዱ በስተቀር ሌላ ዘዴ እንደሌለው የማያውቅ የለም። ይኸም በግል ንብረት ሰበብ ያቀረበው ምክንያት ዋጋ እንደሌለው ግልፅ ነው።

ከጥንት ነገሥታት እንደ አፄ ምኒልክ ያሉት በዚያ የአፍሪቃ ጨለማ ዘመን የዳግማዊ ምኒልክ ት/ቤት መሥርተው ምሑራን አመንጭተዋል። የትምህርት ሚኒስትር የነበሩት እንደነብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ፣ "ጦቢያ" የተባለውን መጽሐፍ የደረሱት እንደነፕሮፌሠር አፈወርቅ ያሉት ሁሉ ከዚህ የትምህርት ቤት የተገኙ ምሑራን ናቸው።

የዳግማዊ ምኒልክን ማተሚያ ቤት አቋቁመው "አዕምሮ" የሚባል ጋዜጣ እየታተመ ለአንባቢ ሁሉ እንዲዳረስ ጥረዋል።

ዲሞክራሲ ባልሠፈነበት በዚያ ጨለማ ዘመን አፄ ምኒልክን ባሽሙር ሲሰድቡ፣ ገጣሚውን ያደንቁታል እንጂ እንደ አክራሪ ኮሚዩኒስት ጋዜጠኞውን ሁሉ ወህኒ ቤት አያጐሩትም ነበር።

ለምሳሌ አፄ ምኒልክን ባሽሙር የተሳደበው የሚከተለውን ገጥሞባቸው ነበር። ቃሉም ጥርስ ገጣጣነታቸውን ይገልጻል "በሰማይ

የሚፀድቅ በምድር ያስታውቃል
ከከንፈሩ ተርፎ ጥርሱ ፀሐይ ይሞቃል"

የትምህርት ሚኒስትሩዋ "ገነት ዘውዴ" ከጌቶቿ በተቀበለችው ትዕዛዝ ያስታላለፈችው አዋጅ ማን ይነካኛል በሚል ዕብሪት ሲሆን፣ በአፄ ምኒልክ ላይ ተገጥሞ የነበረውን ያስታውሰናል። ይኸም ጥንታዊ ቅስቀሳ ለወይዘሮ ገነት ዘውዴ ወደ እናት አገሩዋ እንድታደላ ይረዳታል ብለን በማመን፣

"አባትሽ ምኒልክ፣ እናትሽ ባፈና
አንቺ ማን አለብሽ
በየትኛው ዳኛ አቤት ልበልብሽ"

የተባለውን ግጥም እንድንደግመው ያስገድደናል። የዳግማዊ ምኒልክም ሆስፒታል አይዘነጋም። አፄ ኃይለ ሥላሴ በኢትዮጵያ ውስጥ ትምህርትን ካስፋፉት ነገሥታት የመጀመሪያው ናቸው።

በዘመናቸው አዲስ አበባ ውስጥ የተፈሪ መኰንንን ትምህርት ቤት አቋቁመው፣ ብዙዎቹንም ወደ አውሮፓና ወደ አሜሪካም ተማሪዎቹን በመላክ ብዙ ምሑራን ላገሪቱ አስገኝተዋል። ወደ አሜሪካን አገር ለትምህርት ተልከው ከነበሩት ውስጥ ሐኪሙ ዶክተር መልዓኩ በያንና፣ የትምህርት ሚኒስትር የነበሩት ደጃዝማች መኰንን ደስታ ለመታሰቢያ ያህል ሊጠቀሱ ይችላሉ። ፈረንሣይ አገር የተማሩት ቢትወደድ አንዳርጌና ብላታ ዘውዴ በላይነህም ይታወሳሉ። በየጠቅላይ ግዛቱ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በፊት ትምህርት ቤት አቋቁምው፣ ትምህርት ላልተቋቋመባቸው ጠቅላይ ግዛቶች መምህራን በማስገኘት ትምህርት በየጠቅላይ ግዛቱ ሁሉ እንዲዳረስ አድርገዋል።

ክሊኒኮች ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በፊት በኢሉባቦር፣ በወለጋ፣ በሐረርና በሲዳሞ ሲቋቋሙ ሚሲዮኖችም የየራሳቸውን ክሊኒኮች አቋቁመው አገልግሎት እንዲሰጡ አድርገዋል።

ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ፣ በየጠቅላይ ግዛቱ ከተማዎች የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተቋቁመዋል። በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ወጣት ምሑራን አስገኝተዋል።

በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በመጀመሪያ የተቋቋመው የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ወደ አውሮፓና ወደ አሜሪካ ብዙ ወጣቶች ልኮ በብዙ መቶ የሚቆጠሩ ምሑራን በያመቱ ማስገኘቱ ይታወሳል።

በዚሁ ዓይነት ከየጠቅላይ ግዛቱ ከሁለተኛ ደረጃ የሚመረቁ ተማሪዎች ወደ አሜሪካና አውሮፓ እየተላኩ በልዩ ልዩ ትምህርት እየተመረቁ አገራቸውን ሲገነቡ ኖረዋል።

በጦር ኃይልም ረገድ፣ የሐረር አካዳሚ በመጨረሻው ጊዜ የተቋቋመው ሲሆን፣ በክብር ዘበኛም ከአንደኛ እስከ ሦስተኛ ጊዜ ዕጩ መኰንኖች ተመርቀውበት በተባበሩት መንግሥታት ትዕዛዝ በኮሪያና በኮንጐ የፈፀሙት ታሪካዊ አገልግሎት ዋና ማስረጃ ሆኖ ይኖራል።

በከፋ ጠቅላይ ግዛት ጂማ ውስጥና በሐረርም ጠቅላይ ግዛት የርሻ ኮሌጅ ተቋቁሞ አገሪቱን በዘመናዊ የርሻ ዘዴ በመምራት መሠረት የጣሉ መሆናቸውን ታሪክ ይመሰክራል።

በጤናም ረገድ በጐንደር የጤና ጥበቃ ኰሌጅ ተቋቁሞ ምን ያህል የጤና ጥበቃ ምሑራን እንዳስገኘ ታሪክ ይመሰክራል። በየጠቅላይ ግዛቱም የጤና ጣቢያዎች ተቋቁመው አገልግሎት መስጠታቸው አይዘነጋም።

ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ በብዙ መቶ የሚቆጠሩ የሕክምና ዶክተሮች፣ የልዩ ልዩ ሥራ መሐንዲሶች፣ የሕግና የልዩ ልዩ ትምህርት ሊቃውንት ተመርቀው አገልግሎት ላይ ውለዋል። ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን፣ ለጐረቤት አፍሪቃውያን ሳይቀር አዲስ አበባ ቀዳማዊ

ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ተምረው የተመረቁ ሦስት መቶ አፍሪቃውያን ለዚህ የትምህርት ታሪክ ምስክሮች ሆነው ይኖራሉ።

በተግባረ ዕድም በኩል ከተግባረ ዕድ ትምህርት ቤት የተመረቁ ብዙ ተማሪዎች፣ በልዩ ልዩ ሥራ ላይ ተሠማርተው አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኙ ነበር።

ወደ ገጽ...4.. ይዞራል

ከገጽ ...3... የዞረ

በአሜሪካኖች ተራድኦ ተቋቁሞ የነበረው የአውራ ጐዳና ባለ ሥልጣን የጠቅላይ ግዛቶችን አውራ ጐዳናዎች በመሥራትና በማገናኘት ከፍተኛ አገልግሎት አከናውኗል።

አጭር የኢህአፓ ታሪክ

ከአዲሱ ወሰን

አክራሪው የኮሚዩኒስት ፓርቲ ኢህአፓ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የተቋቋመው ደርግ ሲመሠረት በተቃራኒነት ከመቅጽበት በጐኑ ተሠልፎ ነው።

የኢህአፓ መሥራች የሰሜኑ ተወላጅ "ተስፋዬ ደበሳይ" የሚባለው ሲሆን፣ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ደርግን ክፉኛ ያራውጠው እንደ ነበረ የዚህ ታሪክ አቅራቢ የዓይን ምስክር ነበርሁ በመሐከሉ ብዙ ወጣቶች እገኙበት በነበረው ቀበሌ የኢህአፓ ተከታዮች ናቸው ተብለው ሰታሠሩና ማታውን ሊረሸኑ ሲዘጋጁ፣ "ፀሐዩ" የተባለው ካድሬ የሠፈሩን ሕዝብ ቀስቅሶ ወደ አራተኛ

ክፍለ ጦር ሔደው ለጦር አለቆች እንዲያመለክቱ አደረገ። ከዚያም የጦር ሠራዊት ወታደሮች በከባድ መኪና ተሣፍረው የጦር መሣሪያ አንግተው ወደ ቀበሌው ገቡ። ወጣቱን ሊያስገድል የነበረውን የቀበሌውን ሊቀ መንበር አሥረው ወደ አራተኛ ክፍለ ጦር ወሰዱት። ሊረሸኑ የነበሩት ወጣቶች በሙሉ እንዲለቀቁ ተደረገ።

ደርግ በኢህአፓ መሥራች "በተስፋዬ ደበሳይ" ላይ ምሥጢሩን ሁሉ ደርሶበት ሊያፍነው ሲዘጋጅ፣ እሱም ጉዳዩን የሚከታተል ብልህ ወጣት ነበርና ይኖርበት ከነበረው ከሐራምቤ ፎቅ ላይ ተፈጥፍጦ ራሱን በመግደል ሊሞት ቻለ።

ከዚህ በኋላ "በጀማል አብዱል ናስር" ጊዜ በኮሚዩኒዝም ርዕዮተ ዓለም ግብፅ ውስጥ የሠለጠነው "ብርሃነ መስቀል ረዳ" በትግራይ ውስጥ "አሲምባ" ላይ የኢህአፓ ተዋጊ ጦር መልምሎ የደርግን ጦር እያደባ ይመታ ነበር።

እነዚህም አሁን አዲስ አበባን የያዙት "እነመለስ ዜናዊ" የኢህአፓ አክራሪ ኮሚዩኒስቶች ናቸው። አብረዋቸው የሚገኙትና ቁልፍ የሆኑ መሥሪያ ቤቶችን ይዘው የሚመሩ ሁሉ የብርሃነ መስቀል ረዳ ምልምሎችና ወታደሮች የነበሩ የኢህአፓ ኮሚዩኒስቶች ናቸው። እነዳዊት ዮሐንስ የቀይ ባንዲራ አክራሪ ኮሚዩኒስት እነዮሴፍ ተስፋዬ፣ የትምህርት ሚኒስትሩዋ ገነት ዘውዴ፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩ እነታምራት ላይኔና ሌሎቹም በሙሉ የኢህአፓ አባላት የነበሩ መሆናቸው የአደባባይ ምሥጢር ነው።

ፀረ ኮሚዩኒስት የሆኑትን ሁሉ ደርግ እያደነ በማሠር ያጉላላ ነበር። ምሑራን ባለሥልጣኖችንም እስር ጨፍጭፎቸዋል። ኢህአፓ በተቃራኒት መቅረብ የተቻለውን ያህል እንዲከላከል ረድቷል። ኢህአፓ ደርግን ፋታ በማሳጣቱ ብቻ ልቤ ይረካ ነበር። ሆኖም "እናቴን ያገባ ሁሉም አባቴ ነው" የምል አይደለሁም። ታፍኖ የኖረው አጭር ግጥሜን ግን አቀርብለታለሁ።

ታሪካዊ ግጥም

==========

እነአፄ ቴዎድሮስ፣ ለናት አገራቸው
በኩራት ሲገዙ፣ ጠላት ሳይደፍራቸው
እነአፄ ዮሐንስ፣ መተማ ላይ ወድቀው
አፈር አላስነኩም፣ ሲገዙ እንዲያ ፀድቀው።
እነአፄ ምኒልክ ያፍሪቃው ንጉሥ
በታሪክ አለፉ፣ ሳይገባን ነፋስ።
ተፈሪ.አባ ጠቅል፣ የማይጨው አንበሳ
"ነበር"ሩቅ ኖርዋል ወይ? እንደምን ተረሣ።
የዛሬው አመስጋኝ፣ ጠላታቸው ነበርሁ
ሦስት ዓመት ማቅቄ፣ ከወጣሁ ሰንበትሁ።
ደሳሳ ጐጆ ውስጥ፣ ቆራጥ ልጆች ሞልቷት
መሐን አይደለችም፣ ይህች አገር የኛ እናት
ልቅሶና እንጉርጉሮ፣ በጣም በዝቶበት
ቆራጥ ልጇ ወጣ፣ ሳይሰናበት።
ጐራዴው ከንዳ፣ ወጣና ተሳለ
መሥዋዕት አድርገኝ፣ ለታሪክ እያለ
ሠይፉም ከቆጥ ወርዶ፣ በሞረድ ተሳለ
ዘልቆ ሲያሽሟጥጠው፣ ሙልጭ ሙልጭ አለ።
አማራና ትግሬ፣ ኦሮሞ መባሉ
አለያይቶ መግዛት፣ ዘዴ ነው ይላሉ።
የመረቀዘ ነው፣ የኖረ በሽታ
ካልተባበሩበት፣ አይድንም ባንድ አፍታ።
ደርግን ሳላነሣ፣ እንደምን ልለፍ
የቀይ ሽብር ንጉሥ፣ ያጭበርባሪ ሠልፍ።
በደርግ ሁለት ዓመት፣ በሥር ተንገላታሁ
ኢህአፓ ገንፍሎ፣ ተሠልፎ ወጣሁ።
ባለውለታዬ፣ ነበረ ወጣቱ
ስሜን በመፈክር፣ ገልጾ በማውጣቱ።
በንጉሡም ጊዜ፣ ማቅቄ ስወጣ
ከደርግ ነፍሴ ተርፎ፣ በሥቃይ በቀጣ
ሕዝቡ በሰጠኝ ስም "ቢያርዱት አይሞት" መጣ!።
ራስ መኰንን ድልድይ፣ የፀጉራቸው ማማር
ወይዛዝርት ወጣቶች፣ የሞቱባት አድባር።
ካራት ኪሎ እንስቶ፣ ስድስት ኪሎ ሁሉ
ተዝርሩዋል ወጣት፣ ያገር ልጅ በሙሉ።
ከዚህ ማዶ ልቅሶ፣ ከዚያም ተለቀሰ
ጠቅላላው ሕዝባችን፣ ጥቁር ከል ለበሰ።
የገደለው ባልሽ
የሞተው ወንድምሽ።
ሐዘንሽ ቅጥ እጣ
ከቤትም አልወጣ።
ይሉ ነበር አበው፣ የታሪክ አባቶች
ምን ይሰማችኋል? የትናንት ወጣቶች፣ የዛሬ
አዛውንቶች።
የኢህአፓ መሥራች ተስፋዬ ደበሳይ
ተፈጥፍጦ ሲሞት፣ "ከሐራምቤ" ፎቅ ላይ።
ምን ዓይነት ጀግና ነው፣ ወሳኝ በሕይወቱ
ደርግን የሚቋቋም፣ ነበረ ፍጥረቱ።
ዘር ልዩነት የለም፣ በወጣት ዓለም
ኦሮሞና አማራ፣ ትግሬውም የለም።
ኦሮሞና ትግሬ፣ አማራ መባሉ
ወሬሻም አይችለው፣ ተገንጥሎ አካሉ።
ብርሃነ መስቀል ረዳ፣ የተገደለ ዕለት
ፍፁም ተጠናክሮ፣ ኢህአፓ ባሰበት።ጠቅላይ
መምሪያው ነበር፣ ለኢህአፓ አሲምባ
ደርግን ድል አድርጎ፣ መሐል ሸዋ ገባ።
አባቱ ነበሩ፣ የጦር ሠራዊት
ጀግና ልጅ የተኩ፣ የሚፋጅ እሳት።
መንግሥቱ ኃይለ ማርያም፣ ሲጨፍር ሕዝቡ ላይ
ያጋየው በጥይት፣ አብዮት አደባይ።
ሱራፌል ካባ ነው፣ ታሪክ የመዘነ
በተረሸነ ቀን፣ ሕዝባችን አዘነ።
አክራሪው ኮሚዩኒስት፣ ኢህአፓ ልበለው
ሃይማኖት ግን የግል፣ ሀገር የጋራ ነው።
አማራው ካማራ፣ ትግሬውም ከትግሬ
ኦሮሞሞ ላገሩ አለው ብዙ ፍሬ
ኃይሌ ፊዳም ቢሆን፣ ከፓሪስ ገሥግሦ
መሥርቶ ሚኤሶን፣ ለወጣት ለግሦ።
ደርግን ለመጣል ነው፣ ቀበሌን መሥርቶ
የአብዮት ጥበቃን፣ መሣሪያ አስነግቶ።
በመጨረሻው ግን፣ ደርግ እየሰለለ
ወጣቱም ተመታ፣ ኃይሌም ተገደለ።
ደርግና ኢህአፓ፣ አብዮት ላይ ተዋግተው
አየሁ ብዙ ወጣት፣ በግንባር ተደፍተው።
ለጠመንጃ አፈሙዝ፣ አልበገር ብሎ
ኢህአፓ ድል ነሣ፣ ካሲምባ ገንፍሎ።
ሁለት ኮሚዩኒስቶች፣ ኢህአፓና ደርግ
አክራሪው ድል ነሣ፣ በቡሽ ከዳን ጥግ።
ባፍሪቃ ባውሮፓ፣ ካናዳ አሜሪካ
ወጣት ስደተኛ፣ አምልጦ በጫካ
ሕይወቱን አድኖ፣ ክብሩን ሳያስነካ
ደርግን ድል አድርጎ፣ መግባቱ ነው ለካ።
እንደ ሌባ ሆና፣ እንደ ተገረፈች
ደርግም ግራ ገባው፣ መንጌም ፈረጠጠች።
እኔ ዘር አልጠቅስም፣ ቅይጥ ሐበሻው
ኢትዮጵያን ብቻ ነው፣ እኔ የምሻው
እኗንም ከነኳት ሲሉ ለጥቅማቸው
ሐበሻን ይወቁ፣ ታሪክ ይንገራቸው
በኢ-ት-ዮ-ጵ-ያ ደም፣ የተጠለለ
ሙሴን ያሻገረው ቀይ ባሕር መሰለ።
ዮሴፍም በሕልሙ፣ አይቶት እንደ ነበር
ዳዊት በመዝሙሩ፣ ያደነቃት አገር።
ቀይ ባሕርን ሙሴ፣ በምንት ሳይሻገር
ያች ወደብ የኛ ናት፣ ታሪክ ሳይነገር።
እውነት ነውር ነወይ፣ ማረስ ባገርሽ
ዘልዓለም ልመና፣ እጅ ዘርግተሽ
ነብር ሆይ አዳኝሽ፣ አያዝንም ለነፍሱ
ካልገደልሁ ብሎ፣ አይቀባ ራሱ።
አዳኞቹ ሁሉ፣ አጥተው ሲመለሱ
ሳይገድል አድኖ፣ ተቀባልሽ እሱ
ቢሞትም ቢገድልም፣ ሞኝ ነው ያሰኛል
አድኖ መቀባት፣ ይሻል ይመስለኛል።
ወጣቱም እንደ ጉርፍ፣ አዘቅቱን ይውረደው
ያባቱ ተራራ፣ ምኑም አይጋርደው
እርጅና ምንተዳው፣ ልበ ተራራው
ከወጣት ይብሳል፣ ጊዜ ሲጠራው።
አማራው ባማራ፣ ፓርቲ ውስጥ ተሻጠ
ኦሮሞም እንደዚያው፣ ፓርቲ ውስጥ ተሻጠ
ትግሬም በጥፋቱ፣ ፓርቲ ወስጥ ተሻጠ
ዘር ልዩነት ገብቶ፣ ሕዝቡን በጠበጠ።
እንዳሻው ይበለው፣ ይበለው እንዳሻው
ካልተበጠበጠ፣ አይጠራም ጥቀርሻው።

ኮሙዩኒዝም ቀዘቀዘ፣ ረከሰ፣ ተተፋ።

ኮሚዩኒዝም ሲባል በጣም ጥሩ ነገር ይመስለኝ ነበር። የዕኩልነት መብት አብሳሪ ነው ሲሉ በደስታ ፈነደቅሁ። የግል ንብረት ሲወረስ ሁሉም ሰው ዕኩል ተከፋፍሎ የሚመጣጠን መሰለኝ። መታሰር፣ መገረፍ፣ መገደል መኖሩን አላወቅሁም። መጻሕፍቶቹንም ሳነብ ከማር ይበልጥ ጣፈጡኝ። እስክቀምሰውና እስክዳስሰው ድረስ "ቴዎሪው" ወይም ዕንሰ ሐሳቡ አስፈነጠዙኝ። ማርክስ ስለ እራሱ የሕይወት ታሪክና ሌላውንም እንግሊዝ አገር በነበረ ጊዜ የጻፈውን ሁሉ አነበብሁ።

ሌኒን የማርክስን ምኞት በተግባር ለማዋል ከጻፋቸውም መጻሕፍት ውስጥ ብዙዎቹን መረመርሁ። መልሶ መላልሶ የሚነግረኝ "ውሃ ቢወቅጡት እምቦጭ" የሚለው ያገሬን ተረት ሆነብኝ። በዚህም የሌኒን ሥነ ጽሑፍ ተደናገርሁ። በአዕምሮዬ ተቀርጾ የሚቀር ነገር አጣሁ። ቀደም ሲል በልጅነቴ በማርክሲዝም ቴዎሪ ያልበሰልሁ በመሆኔ ነው የሚል እምነት አደረብኝ። ኮሚዩኒዝም ምን አይነት ጉድ ነው ማለት ጀመርሁ።

ኮሚዩኒዝም ለሊቀ መናብርቱና ለፓርቲ አባሎቹ የማር ወለላ መሆኑን ደረስኩበት። በጠመንጃ አፈሙዝ የፈለጉትን ሁሉ ያገኛሉ። ወርቅ አንጥፈው ይተኛሉ። ከሕዝቡ በወረሱት ንብረት ከውጭ አገር ካፒታሊስት አገሮች ጋር እየተጻጻፉ በተወረሰው ወርቅ ይነግዱበታል። ግንም ሰው እንዲያውቅባቸው አይፈልጉም። አንድ ሰው ይኽንን ድርጊታቸውን አውቆባቸው ቢገኝ ወዲያው ተይዞ ይረሸናል። ስለ ተረሸነው ሰው የሚያወራ ከተገኘ እሱም ተይዞ ይደገማል። ሒደቱ ሁሉ በዚህ ዓይነት የሚቀጥል ሆኖ አገኘሁት።

ይኽንን ሁሉ ካመዛዘንሁ በኋላ፣ ዕድለኛ ነኝና "የጂላስን" መጽሐፍ አገኘሁ "ጂላስ" የዩጐስላቪያ ተወላጅና የኮሚዩኒስት ፓርቲ አባል የነበረ፣ በሞስኮ ክሬምሊን ቤተ መንግሥት ከነፍስ ገዳዩ ከስታሊን ጋር ተገናኝቶ ስለ ሁለቱ አገሮች (ስለ ዩጐስባቪያና ስለ ሶቭየት ኅብረት) ለመነጋገር በመልዕክተኛነት ክሬምሊን ቤተ መንግሥት ስንብቶ፣ በጥናት የጻፈውን "አዲሱን መደብ" የሚል መጽሐፍ አገኘሁ። መጽሐፉን ከዳር እስከ ዳር እንብቤ ጨረስሁት።

አዲሱ መደብ የተባለው ይህ መጽሐፍ የሶቭየት ኅብረት ኮሚዩኒስቶች "መደብ አልባ" መንግሥት እንመሠርታለን ብለው የነበረውን ቀልብሰው፣ ራሳቸው አዲስ መደብ እንደ መሠረቱ ያረጋግጣል። ይኸውም አዲሱ መደብ የተባለው መጽሐፍ ሲተነተን፣ የመስኮብ ኮሚዩኒስት ፓርቲ አባሎች ምን ዓይነት አዳዲስ የካፒታሊስት አገር አውቶሞቢሎች እንደ ገዙ፣ ምን ዓይነት ሕንፃዎች ለመኖሪያ እንደሚያሳንፁ፣ በየመኖሪያ ቤታቸውም ውስጥ ከካፒታሊስት አገሮች የሚያስመጧቸውን የቤት

ዕቃዎች ዓይነትና ብዛት ተንትኖታል።

በዚህ ዓይነት የሶቭየት ኅብረት ኮሚዩኒስት ፓርቲ አባላት በያሉበት ግዛትና አውራጃ ሁሉ ሽሙንሙኖችና ሽቅርቅሮች መሆን እንደ ጀመሩ በዝርዝር ገልጸውታል። በጠቅላላው የሶቭየት ኅብረት ኮሚዩኒስቶችና ሌላውም የዚህ ዓላማ ተከታይ ዓለም የንጉሠ ነገሥት መንግሥት እየገለበጡና መደብ አልባ መንግሥት እንመሠርታለን እያሉ የሚያጨበረብሩ አዲስ ወሮበሎች በዓለም ዙሪያ መነሣታቸውን ዘርዝሮታል። እነዚህም በዓለም ዙሪያ በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኙት ወሮበሎች የሕዝቡን ደም የሚመጥጡና ንብረቱን ወርሰው ለራሳቸው ጥቅም የሚያውሉ አዲስ መደብ መመሥረታቸውን አጋልጧል።

ስለ ኮሚዩኒዝም ብዙ በእንግሊዝኛ የተጻፉ መጻሕፍት አንብቤ ልረካ ያቃተኝን ያህል፣ አዲሱ መደብ የተባለው የጂላስ መጽሐፍ ስለ ኮሚዩኒስቶች አጭበርባሪ ሑደት ባጭሩ አስተማረኝ። ከዚህ በኋላ ከዕንቅልፌ ነቃሁ። በእግሬ መቆሜን አመንሁ። ' ኮሚዩኒዝም ምን እንደ ሆነ ለይቼ አወቅሁ። እስከዚህ ጊዜ ድረስ ግን ፍፁም ጅል ነበርሁ። ሌሎቹ መጻሕፍቶቻቸው ቀል አድርገውኝ መጨበጫ አሳጥተውኝ ኖሩዋል።

ታላቁ የአሜሪካን ሕዝብና መንግሥት ኢትዮጵያን በርሃብና በቸነፈር ስትገረፍ በመሐከሏ ተገኝተው እንደ ረዱት ሁሉ፣ ኢትዮጵያን ከኮሚዩኒዝም መንጋጋ ፈልቅቆ ለማውጣትም ረድተዋታል። አሁንም ቢሆን ከአክራሪው የኢህአፓ ወያኔ የኢትዮጵያ ሕዝብ በራሱ ትግል በቅርቡ እንደሚገላገል እርግጠኞች ነን። ኢትዮጵያዊ ሁሉ የራሱን ዕድል በራሱ ለመክፈት ዝግጁ ሆኖ በኅብረት ተሠልፏል።

ሶቭየት ኅብረት ተብሎ ይጠራ የነበረው በኃይል ብቻ በመጠቀም በሰባ አራት ዓመታት ሕዝቡን ከመጠን በላይ ሲአሠቃይ ኖረ። ስታሊን የተባለው ግፈኛ ነፍሰ ጉዳይ ሃያ ሚሊዮን የሚሆን የራሱን ወገኖች ፈጀ።

የስታሊን ተከታይ "ኒኪታ ክሩስቾቭ" ደግሞ በሕዝብ ላይ ተተብትቦ የነበረውን ሰንሰለት ጥቂት ቢያላላም፣ የሥልጣኑ ተቆጣጣሪ የነበሩት ግራ አክራሪዎች ወዲያው ከሥልጣን አውርደው ገደሉት።

ጊዜ ራሱን ቆጥሮ ሲመጣ "ሚካኂል ጐርባቾፍ" ወገኖቹን ሰብዓዊ በሆነ መሥመር ለመምራት ሲጥር፣ የሥልጣኑ ኃይል ፓርቲውንና ሕዝቡን አለያይቶ ገንጥሎ ጣለው። ትክክለኛ ያልሆነ ነገር ሁሉ ጊዜ ይቆጥራል እንጂ አይቆይም። ውድቀቱም ጊዜ አይፈጅም። ይህ በዚህ ዓይነት መከናወኑ ላይቀር፣ ጥቂት ምዕራባውያን አገሮች ሶቭየት ኅብረትን ለብዙ ዘመናት ሲፈሩ ቆዩ። ምናልባት ቀዝቃዛው ጦርነት ሶቭየት ኅብረት ታወጣ የነበረውን የተርከፈከፈ የመከላከያ ወጪና የቦምቡ ክምችት፣ የፖለቲካውና ወታደራዊው ንቅናቄ ሁሉ አሥግቷቸው ይሆናል። ዓለም አቀፍ ኮሚዩኒዝም እየተባለ እንደማይደፈር አድርገው ያመልኩበት የነበረው ኮሚዩኒዝም ስሕተት መሆኑ ተረጋገጠ።

ክሩስቾቭ "እንቀብራችኋለን" ብሎ በአሜሪካን ሕዝብና መንግሥት ላይ ያደረገው ዛቻ ተገልብጦ፣ እንደ አገሬ ተረት "እትዋል ይዋሉ፣ አትምከር ይምከሩ፣ በቆፈሩት ጉድጓድ ሳይገቡም አይቀሩ" የተባለውን ሆነው አረፉ።

የራሱን ወገኖች መሥዋዕት የሚያደርግ ማንኛውም መንግሥት ለሌላው ሁሉ አደገኛ መሆኑ ስለማይካድ፣ ምዕራባውያን እንደ አመጣጡ ተቋቋሙት። በመጨረሻም ድባቅ መቱት። በሌኒንና በስታሊን ተመሥርቶ የነበረው የማርክሲዝም ዕንስ ሐሳብ፣ እነሱ እንደ ተመኙት ሳይሆን፣ ውስጡ የሚገኙት ባለሥልጣኖች እርስ በርስ ተጋጭተው ሊፈራርሱ ቻሉ።

በማዕከላዊ ፖለቲካና ኢኮኖሚ ቁጥጥር ላይ ተመሥርቶ ጠቅላላ ቋሚነቱንና እምነቱን በኮሚዩኒስት ፓርቲ ላይ ጥሎ ያካሔድ የነበረው መንግሥት እጀ ሰባራ ሆኖ ቀረ። ከሌላው ዓለም ጋር እንዳይወዳደር ኋላ ቀር ከመሆኑም በላይ፣ ምሥራቅ አውሮፓ ይገኙ ለነበሩትም ተከታዮቹ በፖለቲካ ረገድ ደካማነቱን አስመዘነ። ውጤቱም በሶቭየት ኮሚዩኒዝም ላይ በራስ መተማመን አለመኖሩን አረጋግጦ መግቢያ መውጫ መንገዱን ዘጋ። ዲሞክራሲ ባደረገው እሳት ለበስ ቁጥጥር ድል መታ። እምባ ገነንነት ፍሬ ቢስ መሆኑ ተረጋገጠ። የመሻሻል እምነት ግፈኞችን አንበረከካቸው።

የሶቭየት ኅብረት ሁኔታ ለኅብረተሰቡ ምርምር ሆኖ ግማሹን ዓለም በሥጋት ላይ ጣለው። የነገሥታትን አስተዳደር በመደምሰስ የዓለም ጦርነትንና የርስ በርስ ደም መፋሰስን አስከተለ። የዕኩልነትን ሙብት በማንተራስ የግል ንብረትን ወርሶ ለራሱ ጥቅም አዋለ። ይኸም ሁሉ ተጠቃሎ ደካማነቱን አስመዘነበት።

በሁለተኛው ዓለም ጦርነት የናዚን ጦር ድል ከመቱት ውስጥ የሶቭየት ኅብረት ሠራዊት አንዱ ነበር። እንደ አውሮፓ ዘመን አቆጣጥር በ1949 የሶቭየት ኅብረት የአቶሚክ ቦምብ ሠራች። እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1961 "ዩሪ ጋጋሪን" የተባለውን የመጀመሪያ ሰው ወደ ጠፈር ላከች። በ1956 ክሩስቾቭ ንግግር ሲያደርግ ብትወዱም ባተወዱም ታሪክ ከኛ ጋር ነው ሲል ፎከረ። ባለታሪክነቱ ቀርቶ አገሪቱና ተከታዮቿ ፈራርሰው እንዳልነበረ ሆኑ።

ከመጀመሪያው ጊዜ አንሥቶ የሶቭየት ባለሥልጣኖች ደም በማፍሰስና በከፋት ወገኖቻቸውን ለሥቃይ የዳረጉ ናቸው።

እንደ አውሮፓ ዘመን አቆጣጠር በ1929 ስታሊን በገበሬዎች ላይ የገባር ዓይነት አስተዳደር ፈጥሮ አብዛኛውን ያገሪቱን ገበሬዎች ወደ ኅብረት እርሻ አስገማራቸው። ገበሬዎቹ በእምቢታ ሲቃወሙትና ሲቋቋሙት በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩትንና "ጐላግ" ተብለው የሚጠሩትን ከበርቴ ገበሬዎች ከንብረታቸው ላይ አንስቶ ወደ ሣይቤሪያ እንዲሰደዱ አደረገ። በዚህም ምክንያት የሶቭየት ኅብረት ሕዝብ እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1932 በከባድ ረኃብና ቸነፈር ላይ ወደቀ። የኅብረት እርሻ ሲታወጅ አሥራ አንድ ሚሊዮን በነበረው ነቀፋ፣ ተቃዋሚዎቹ "ጐላግ" ከተባሉት የገበሬ ከበርቴዎች ጋር አብረው እንዲደመሰሱና ከዓይኑ ፊት እንዲጠፉ አዘዘ።

በዚህም ወቅት ስታሊን ራሱን በራሱ በማታለል "የአንድ ሰው ሞት አሣዛኝ፣ የብዙ ሕዝብ እልቂት ግን ስታቲስቲክስ ነው" ሲል ተናገረ፣ የስታሊን ወንጀል በክሩስቾቭ የተጠቀሰ ቢሆንም፣ በመጨረሻ ጊዜ ግን በጐርበቾፍ ተደመደመ። ከስታሊን ግዲያ የተረፉትም ለብሬዥኔቭና ለተከታዮቹ የመቃብር ሳጥን አዘጋጁ።

ምዕራባውያን ሶሺያሊስቶች በሶቭየት ኮሚዩኒዝም ላዩ ፊታቸውን ማዞር የጀመሩት እንደ አውሮፓ ዘመን አቆጣጠር በ1930ዎቹ ዘመናት ሲሆን፣ ይኸውም ሊታወቅ የቻለው ስታሊን ይፈጽም የነበረው የፍትሕ መዛባት በግልጽ ስለ ታየና ሕዝቡን ከዳር እስከ ዳር ሊቀሰቅስ በቻለ ጊዜ ነበር። በብሬዥኔቭ የውዥንብር ዘመናት ሳይቀር ዳብዛው ሊጠፋ ተቃረበ። መራራ በሆነ ቁጥጥርና የዕኩልነት ውዥንብር ገድያ ተንተርሶ ግለሰቡ ከቁጥጥር ውጪ ሆነ። አዕምሮ ሳያመዛዝነው ችጋርን የሚካፈልበት ዕድል ተተካ። ማዕከላዊው ሥልጣን ኢኮኖሚውን አቃውሶ የየአገሩን ጐሣ ጠብ ሲጭር እንደ አውሮፓ ዘመን አቆጣጠር በ1962 በኪዩባው ሚሣይል ምክንያት ክሩስቾቭ የአገሪቱን የፖለቲካ መንፈስ አቃወሰ። በዚሁ ዘመን ውስጥ ሶቭየት ኅብረት ከመጠን በላይ የሆነ የጦር ኃይል በመገንባቷ ሕዝቡን ድህነት ላይ ጣለችው። ከሶሺያሊስት አገሮች ጋር በወንድማማችነት ስም በመግባባት፣ በ1956 ከሐንገሪ ጋር፣ በ1968 ከቼኮስሎቫኪያ ጋር ኅብረት ፈጠረች። ከሬምሊን ከዚህ ቀጥሎ አንድ ሌላ ድልድይ ተሻግሮና ርቆ፣ "አፍጋኒስታንን" ለመጨመር በመሞከሩ፣ በማያፈናፍን አለት ድንጋዮች መካከል ገብቶ ተቀበረ። የዚህም ውጤት እንደ አውሮፓ ዘመን አቆጣጠር በ1985 ጐርባቾፍን ቡሥልጣን ኮርቻ ላይ አውጥቶት፣ በጥቂት ጊዜ ውስጥ ኮሚዩኒዝምን በሕዝብ ጀርባ ላይ ከማስቀመጥ ይልቅ፣ ከሕዝብ ጫንቃ ላይ አውርዶ እንክትክቱ እንዲወጣ ማድረግን መረጠ። በዚህም ቆራጥ ድፍረቱ ዓለም ከኮሚዩኒዝም ስጋት ነፃ እንድትወጣ አድርጐ ራሱ ግን ከሥልጣን ወርዶ ተሰናበተ።

ከደርግና ከወያኔ ጋር የተደረጉ ጦርነቶች

ይህ ከዚህ በታች የተጻፈው አስደናቂ ታሪክ "ከምሥራቅ ኢትዮጵያ ብሔራዊ ጦር አዛዥና ሕዝባዊ ጦር አስተባባሪ የተገኘ ነው።" የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ብሔራዊ ጦር አዛዦች የደርግን በኢትዮጵያ ዙፋን ላይ መቀመጥ በመቃወም፣ ዋድላ ደላንታ፣ በዋግ፣ በላስታ ላሊበላ፣ በብልበላ ጊዮርጊስና በብልበላ ቂርቆስ፣ በሣርዝና ሚካኤል፣ በማዕይ ማርያም፣ በዓይና ቡግና፣ በአቡነ ዮሴፍ፣ በአንጃፋት፣ በግዳን፣ በመቄት፣ ትግሉ ተመሠረተ። ትግሉንም የመሠረቱት ግራዝማች ጉግሳ አንባው (በኋላ ራስ) ሻለቃ ወንዴ ታየ (በኋላ ደጃህማች) የግራዝማች የማኑ አቤው ልጆች ቂኛዝማች ታፈረ እጅጉ (በኋላ ደጃዝማች) ሻለቃ በላይ አሊጋዝ (በኋላ ደጃዝማች) ሻለቃ ወሌ ታደሰ (በኋላ ደጃዝማች) የመቶ አለቃ አለማየሁ ወረኛ (በኋላ ፊታውራሪ) አቶ ዱባለ ምን ይሉ (በኋላ ሻለቃ) አቶ በቀለ ዘውዴ (በኋላ ደጃዝማች) ግራዝማች አበራ በላይ (በኋላ ደጃዝማች) ልጅ መለሰ አየለ (በኋላ ደጃዝማች) አቶ ከበደ ምሕረቴ (በኋላ ፊታውራሪ) ነበሩ።

ከዚያም በኋላ ለሁለተኛው ጊዜ የጦር ስብሰባ፣ ብሔራዊ ጦር ለበላይ አዛዥነት ሕዝባዊ ሠራዊት ተመሠረተ። ለዚህም ጦር መምሪ "ራስ ብርሃነ መስቀል ደስታ" የበላይ አዛዥ ሆነው ተሾሙ።

በሦስተኛው ጊዜ በተደረገው የጦር ስብሰባ፣ ባገሪቱ ባህልና ወግ መሠረት፣ በብሔራዊ ጦርና በሕዝባዊ ጦር፣ የሚመራ፣ የጐበዝ አለቆች፣ ያገሬው ባላባት ተወላጆችና የመሳፍንት ዘሮች፣ የሃይማኖት መሪዎች፣ አገረ ገገርዎች፣ የፍርድ ቤት ዳኞች፣ የመንግሥት ባለሥልጣኖች፣ የፓርለማ አባሎችን ሁሉ በማደራጀት፣ ሕዝባዊ አመፅ ተቀነባበረ። ከዚህም በኋላ መደበኛ ሠራዊት ተዘጋጅቶ ከሠላሳ ሺህ ጦር በላይ ለውጊያ ቀረበ።

ወደ ገጽ..6. ይዞራል

ኢትዮጵያዊው ጀግና ‹ሡልጣን› ንጉሥ አሊ ሚራህ የአፋር አርባኛና የጀግናው ሕዝብ ንጉሥ ናቸው።

ከገጽ ..5.... የዞረ

ከወሎ ዙሪያ እነፊታውራሪ በላይ ዘለለው (በኋላ ቢትወደድ ራስ) ፊታውራሪ አሰፋ ታረቀኝ (በኋላ ደጃዝማች) ፊታውራሪ አሰፋ እንግዳ (በኋላ ደጃዝማች)፣ ፊታውራሪ መኩሪያ ዘገየ (በኋላ ጃዝማች)፣

ከጐንደር ቢትወደድ አዳነ መላኩ (በኋላ እራስ ቢትወደድ)፣ ቀኛዝማች አድማሱ በላይ (በኋላ ደጃዝማች)፣ ባላምባራስ ባዛብህ አደመ (በኋላ ደጃዝማች) ከጐጃም ቀኛዝማች ትርፌ (በኋላ ደጃዝማች)

ከሸዋ ልጅ መርዕድ ብሩ፣ (በኋላ ራስ) ልጅ ታደሰ ብሩ (በኋላ ራስ) ደጃዝማች ፀሐዩ ዕንቍ ሥላሴ (በኋላ ራስ ቢትውደድ) ቀኛዝማች ታደሰ ዕንቍ ሥላሴ (በኋላ ደጃዝማች) ደጃዝማች ከበደ ብዙነሽ (በኋላ ራስ) የደርግን ሠራዊት በየአቅጣጫው ተቋቋሙት።

ከአፋርና ኢሳ መሪዎች ሡልጣን ቢትወደድ አሊ ሚራህ ሐንፍሬ (በኋላ ንጉሥ)

ከአሥራ ሁለቱም ጠቅላይ ግዛት በመላላክ ንጉሠ ነገሥቱ ከዙፋን ሲወርዱ፣ በላስታ ውስጥ ግንቦት 23 ቀን 1966 ዓም የጦር ክተት አዋጅ ታወጀ። ይኸውም ንጉሠ ነገሥቱ ከዙፋን ወርደው በመታሠራቸው፣ ባለሥልጣኖቹም በሙሉ እየተያዙ ከታሠሩ በኋላ ስለ ተረሸኑ፣ የላስታው ሕዝብ በደርግ ላይ ጦርነት ከፈተ። የሦስት ወረዳ ምሽጐች ደምስሶ፣ የላስታን አይሮፕላን ማረፊያ ተቆጣጠረ። በዚሁ ጊዜ ወስጥ አንድ የጦር መሣሪያ መጓጓዣ አይሮፕላን አቃጠለ። ይኸው ሠራዊት በላስታ የሚገኘውን የደርግን ሠራዊት ተዋግቶና ድል አደርጐ ሲገባ፣ በግፍ ታሥረው የሚሠቃዩትን ዕሥረኞች አስፈትቶ በነፃ ለቀቃቸው። ከዚህም በኋላ በድል አዶራጊነት ላሊበላን ሊቆጣጠር ቻለ።

ከላስታ ጦርነት በኋላ፣ በበጌምድር፣ በጐንደር፣ በደብረ ታቦር በሰሜን አርማጭሆ፣ በወሎ፣ በአምባሰል፣ በዋድላ ደላንታ፣ እንዲሁም የደርግ ጦር በዘመናዊ የኮሚዩኒስት አይሮፕላን እየተረዳ ለሦስት ዓመታት በተለያዩ ሥፍራዎች የብዙ ሕዝብ ሕይወትና ንብረት ለማጥፋት ቢችልም በዋድላ ድላንታ አርሶ አደር ገበሬ ላይ የጣለው የመርዝ ቦምብ የሚዘነጋ አልነበረም። ሕዝቡ የእርሻ ተግባሩን አከናውኖእህሉን አምርቶ ለምግብ በሚጠቀምበት ወቅት በመርዙ የተበከለው ዕህል፣ የሕዝቡን ሕይወት ለማጥፋት ችሏል። በዋድላ ደላንታ፣ ባላስታ፣ በዋግ በበጌምድርና በደሴም ዙሪያ የሚገኘው አርበኛ የደሴን ከተማ ለመቆጣጠር ከዋድላ ደላንታ ተነሣ። ከዚያም በወገል ጤና ላይ ይገኝ የነበረውን የደርግ ጦር ደምስሶ የደሴን ከተማ ለመያዝ ሠላሳ አምስት ኪሎ ሜትር ሲቀረው፣ በኩታ በር ላይ መሽጐ የነበረው የደርግ ሠራዊት፣ በጦር አይሮፕላንና በታንክ ታጅቦ፣ በዓየር ወለድ ሠራዊቱም እየተረዳ በተካሔደው ከፍተኛ ጦርነት ከሃያ ሺህ ሕዝብ በላይ የረገፈበት የጨለማ ዘመን መሆኑን ታሪክ ሊዘነጋው አይችልም።

በኩታ በር ጦርነት ሕይወታቸውን ለእናት አገራቸው የተሠውትን ጀግኖች የደርግ ፋሺስታዊ ሠራዊት አንገታቸውን ቆርጦ ለሕዝብ መቀጣጫ የሚሆን መስሎት በዕንጨት ላይ እየሰካ በደሴ ዋና ከተማ ላይ ያዞራቸው የጦሩ ፊታውራሪ በላይ ዘለለው (በኋላ እራስ ቢትወደድ)፣ ፊታውራሪ አሰፋ ታረቀኝ (በኋላ ደጃዝማች)፣ የታሪክ ጀግኖች ነበሩ። በኋላም (ራስ) ጉግሣ አምባው የላስታ ዋግ ሕዝባዊ ጦር አዛዥ በሊማሊሞ ገደል በሔሊኮፕተር ከጣላቸው ጀግኖች ውስጥ፣ የሕዝባዊ ሠራዊት ጦር አዛዥ የነበሩት "ዱባለ ምን ይሉ ተይዘው ከአንድ መቶ ሰማኒያ ጀግኖች ጋር ተረሽነዋል። ይህ ሁሉ መስዋዕትነት እስታዋሽ ቢያጣም፣ ታሪክን ብቻ መሠረት በማድረግ አንድነቱን አጠናክሮ ሲታገል በሱዳን በኩል በንጉሠ ነገሥቱ ስም "ኢ.ዲ.ዩ" ተመሠረተ ሥራውንና ዓላማውንም ሕዝቡ ሊያውቀው አልቻለም። በተለያዩ የጦር መልዕክቶቹም ባደረገው ግንኙነት የአርበኛውን ትግል እናጋው ኢ.ዲ.ዩ ለአርበኛው ሠራዊት አዲስ ስም ስለ ነበረ ለታሪክና ለባህል ዕንግዳ ነገር ሆኖበት ግራ አጋባው።

ይኸንንም የኢ.ዲ.ዩ ፓርቲ ለመመሥረት በተደረገው መመሪያ ግማሹ ጦር ሲቃወም፣ ግማሹ ዕርዳታ ማግኘት አስፈላጊው ስለ ነበረ፣ የአርበኛው ሠራዊት በሁለት ክፍል ተከፈለ ዕርዳታ ማግኘት ያስፈለገው አርበኛ ሠራዊት ሱዳን ጠረፍ ላይ ተከማቸ።

ከዚህ በኋላ፣ የኤርትራና የወያኔ አክራሪ ኮሚዩኒስቶች በኢትዮጵያውያን አርበኞች ላይ ተባብረው ጉዳት ሊያደርሱ ቻሉ። በዚሁ ጊዜ ወደ መሐል አገር ለመግባት ዕድል አገኙ። የደርግ ሠራዊትም በበኩሉ በአርበኞቹ ላይ አደጋ ሲያደርስ፣ በቂ የጦር ዕርዳታ ማግኘት አስፈላጊ ስለ ሆነ አርበኛው ሠራዊት ተመካክሮ ወደ አፋሩ ሡልጣን ቢትወደድ አሊ ሚራህ ዘንድ በመጓዝ "ከአፋር ጦር" አርበኛ ሠራዊትና ከአፋር ሕዝብ ጋር ተቀላቀለ። ሠራዊቱም በዚህ አገር እንደ ደረሰ ዕርዳታ ጠየቀ። ይህ አርበኛ ሠራዊት የሚያገለግለው በንጉሠ ነገሥቱ ስም ለኢትዮጵያ ዙፋን ስለ ሆነ፣ መልሱን ማግኘት የሚቻለው ለንደን ወስጥ ይገኙ ከነበሩት ከልዑል አልጋ ወራሽ አስፋ ወሰን ስለ ነበረ፣ መልሱን ተጠባበቁ ተባለ። ጦሩም በአፋርና በመሐል አገር እንደ ተከማቸ ሆኖ መልሱን ሳያገኙ ለሦስት ዓመት ያህል መቆየት ግድ ሆነባቸው።

ክቡር ራስ ቢትወደድ አዳነ መላኩ የበጌ ምድር ጀግና የታሪክ ባለቤት ነበሩ ለንጉሠ ነገሥታቸውና ለሀገራቸው ያደረጉት ታላቅ ተጋድሎ በኢትዮጵያ ታሪክ ለዘላለም ሲታወስ የናራል።

የደርግ ጦር በዚህ ጊዜ እየገፋ መጣ። አርበኞቹ አማራጭ አጡ። የሻቢያና የወያኔ ኮሚዩኒስት (ኢ.ህ.አ.ፓ) የጋራ ጠላትን በጋራ መምታት በማለት አርበኛውን ሠራዊት ድልድይ አድርገው ተሸጋገሩ። አሁንም በአርበኞቹ ደምና መስዋዕትነት ተጠቅመው የኢትዮጵያን አንድነት በመፈታተን ላይ ይገኛሉ። ለዚህ ሁሉ ተጠያቂውና ኃላፊው ዘውዱ መሆኑን ልዩው ጽ/ቤት ያምንበታል።

ጦሩ፣ ሠራዊቱ፣ ሕዝቡ፣ አንድነቱ፣ ባህሉና ታሪኩ የሆነውንና፣ ለሦስት ሺህ ዘመናት መመኪያና መከበሪያ ሆኖ የኖረውን ታሪካዊ ዘውድ ለማጥፋት የተነሱትን ጠላቶች የኢትዮጵያ አርበኞች በየአቅጣጫው ተቋቋሙ። ንጉሠ ነገሥቱም ይኸንኑ ጥፋት ተረድተው ለጦሩ አስቸኳይ ዕርዳታ እንዲቀርብለት ፈለጉ። አርበኞቹም በጦሩ ስም ለንጉሠ ነገሥቱ አቤቱታ ካቀረቡ በኋላ፣ ንጉሠ ነገሥቱ አቤቱታውን ተከብለው በለንደን ጠቅላይ ምክር ቤት ከፍቱ። በዚሁ ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱ ክቡር አቶ ዘነበ ኃይሌንና ክቡር አቶ ተክሌ ሮሮ ጂቡቲ ድረስ እንዲሔዱ አዘዙ። እነዚህም ሁለት መማክርት ከአርብኞቹና ከክቡር ሡልጣን አሊ ሚራህ ሐምፍሬ ጋር መመካከር ጀመሩ። ከዚህ በኋላ የንጉሠ ነገሥቱን ጠቅላይ ምክር ቤት የሚወክል ዓምድ አሥር ቅርንጫፍ ምክር ቤት ጂቡቲ ውስጥ ተከፈተ።

ይኸም በጂቡቲ የተከፈተው ጠቅላይ ምክር ቤት ባወጣው መመሪያ የተበተነውን ሠራዊትና የወደቀውን መንፈስ አድሶ በክቡር ቢትወደድ ሡልጣን አሊ ሚራህ ሐምፍሬ ከፍተኛ ድጋፍና ባፋር ሕዝብ ዕርዳታ የሠራዊቱ ትግል ሁለተኛ ምዕራፉን ጀመረ። የአፋርም መሪና ሕዝብ የኢትዮጵያ ታጋዮችና ባለውለታዎች መሆናቸው ተረጋገጠ። ይኸም በጂቡቲ የተከፈተው ምክር ቤት በሀገር ውስጥ የሚገኙትን አርበኞችና ሕዝብ አስተባበረ። በውጭ አገር ሚገኙትን ኢትዮጵያውያን በዘውድ ሥር አሰለፈ። ሕዝቡ የሚመክርበት ሸንጐ የዘወድ ምክር ቤት አቋቋመ። ስለ ዘውድ ወራሴ መንግሥት ስርአት አፈጻጸም መሠረተ። የዘውድም መሠረት የአርበኛውን ጠቅላላ መንፈስ ቀሰቀሰ።

ወደ ገጽ..7. ይዞራል

የምስራቅ ኢትዮጵያ አርበኞች በጅቡ ገብተው የንጉሠ ነገሥቱን ጠቅላይ ምክርቤት ሲመስርቱ።

የአፋር ጀግኖ ች ከደርግና ከኢትዮጵያ ተገነጣዮች ጋር ለመዋጋት ሲዘጋጁ።

የኢትዮጵያ አርባኞች በአጋግ በረሃ መሣሪያቸውን አጥምደው ጠላትን ለመቋቋም ዝግጅት ሲያደርጉ።

የጃንሆይ መግለጫ፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ!

የብዙ ጊዜ ነፃነታችን፡ ባህላችን፡ ታሪካችን አንድነታችን ሥልጣኒያችንና ሥነ ጽሑፉችን በዓለም ከታወቁት አገሮች ውስጥ አንዱ መሆኑን ታሪክ መዝግቦንና ቦታ ሠጥቶን የአንባብያንን ትዝታ እንደማረክነው እንገኛለን።

የደስታ፥ የብልፅግና ዘመን የመኖሩን ያህል የኀዘን፡ የሰቆቃውም ዘመን ባንጻሩ አለ። ይህም በአንድ ሕዝብ ላይ ያለና የነበረ ነው። ከታሪክ እንደምንገነዘበው የሮም መነሳትና መውደቅ እንዲሁም የጀርመን ኃይል በዓለም ላይ ተጠቃሽ ምሳሌዎች ናቸው።

በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥም የዮዲት አገዛዝ፡ የግራኝ ወረራና የኢጣሊያን ሠብሮ ገብነት በተለይም ለአሥራ ሰባት ዓመት በኢትዮጵያ ላይ የነበረው የኮሙኒስት ዝርፊያ ተጠቃሽ የመከራ ዘመናት ናቸው።

የዓለም ሕዝብ ለምርምር፡ ለፈጠራ፡ ለልማት እጅግ በሚረባረብበት ወቅት የኢትዮጵያን ሕዝብ ለአሥራ ሰባት ዓመት በሰዓት እላፊ ገደብ አሥሮ፡ የግል ንብረትን ወርሶ፡ አዋቂዎችን አጥፍቶ፡ ያላቸውን አሥሮና አዋርዶ ሕዝቡን በጐሣ፡ በቋንቋ፡ በሃይማኖት፡ ሁሉ ከፋፍሎ አንድነቱን አሳጥቶ ርስ በርሱ በማፋጀት የራሱን የአገዛዝ ዕድሜ ለማራዘም አዋጅን በአዋጅ ሲሠርዝ ሲደልዝ ሕዝቡን በሐሰት ሲደልል ይህን ያህል ጊዜ ቆየ። ይህም በሕዝቡ ላይ ያስከተለው ለውጥ በዘር፡ በሃይማኖት ርስ በርሱ እንዲጣላ የጥላቻን አውታር በመዘርጋት ልጆች በወላጆቻቸው፥ ወላጆች በልጆቻቸው ጠላትነት እንዲጠነክር ሆነ ብሎ አባቶችን አድኃሪ፡ ኋላቀር፡ ወጣቶችን ተራማጅ፥ ለራሱ ዓላማ ያልተሠለፉትን ቀኞች፥ ግራ አክራሪዎች ወዘተ ... የሃይማኖት ተከታዮችን ሃሳባውያን፡ ጉታቾች፥ ነጋዴዎችን ስግብግቦች በማለት ገበሬዎችንም እንዲሁ ያልሆነ ስም በመስጠት ፀንቶ የነበረውን አንድነቱን፥ ባህሉን፥ ፍቅሩን አናግቶና አጥፍቶ ይህ ነው ከማይባል መከራና ችግር ላይ ሕዝቡንና አገሪቱን ጥሏል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ!

በኢትዮጵያ ምድር እንደ ጉርፍ የሚፈሰው ደም በመንጠፍ ላይ ነው። በኢትዮጵያ አንድነት፥ ሰላም፥ ብልፅግና፥ ዲሞክራሲ፥ ፍፁም ወንድማማችነትና፥ ገናና ታሪክ የሚታደስበት ቀን በመንጋት ላይ ነው። ይህን ጊዜ፥ ይህን ወቅት እንደ ርግብ የዋሆች እንደ እባብ ብልሆች ሆናችሁ በጥንቃቄ እንድትይዙት አደራ እንላለን።

የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደ ነብር መልክ ዥንጉርጉር ነው። ኅብረ ቀለምነት የውበትና የጌጥ እንጂ የልዩነት ማሳያና መታወቂያ አይደለም፥ አይሆንምም። ይህን በጥሞና መገንዘብ አለብን።

ይልቁንስ የሕዝቡን ጉሥቁልና ተመልክቶ የኢትዮጵያን ልመናና ጸሎት አዳምጦ ከዚያ የመከራ የጭንቅና የሥቃይ ሕይወት ውስጥ ሳወጣን ሁሉን ለማድረግ ለማይሳነው ለኃያሉ እግዚአብሔር ምሥጋና እናቀርባለን።

በኢትዮጵያ ላይ በደረሰው ችግር ከፍተኛ ድጋፍና አስተዋጽዖ ላደረጉልን ለምዕራባውያን መንግሥታት በሙሉ እጅግ ጥልቅ የሆነ ልባዊ ምሥጋናችንን እናቀርባለን። የኢትዮጵያ ሕዝብ ለምዕራባውያን አገሮች ልዩ የሆነ አክብሮትና ፍቅር አለው። በችግሩ፥ በመከራው ሁሉ በቅርብ በመገኘት ርዳታቸውን አድርገውለታልና ነው። በተለይም የአሜሪካ ሕዝብና መንግሥት በዓለም ላይ ሰላምና ዲሞክራሲ እንዲጠናከሩ የማድረግ ዓለም አቀፋዊ ኃላፊነትና አደራ ባሁኑ ወቅት ከታሪክና ከእግዚአብሔር መቀበሉ ግልጽ ነው። ይህንኑም ኃላፊነትና አደራ በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ ለማስረፅ በከፍተኛ ደረጃ ሕዝቡ ይጠብቃል።

የኢትዮጵያና የአሜሪካ ሕዝብ ወዳጅነት ቀደም ሲል ፀንቶ የቆየ ነው። አሁንም አለ። ወደፊትም ይቀጥላል። ከዚህ ላይ ማውሳት የምንሻው በ1954 ዓ ም እ፡አ፡አ፡ ገና የአፍሪቃ አገሮች በቅኝ ግዛት በነበሩበት ወቅትና ለጥቂት አገሮች ብቻ መሪዎች ክብር የሚደረገውን ለአባታችን ለገርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በዋሺንግተን ዲሲ ተገኝተው ለጋራው የኮንግሬሱ ስብሰባ ንግግር እንዲያደርጉ መጋበዛቸው በኢትዮጵያና በአሜሪካ መካከል የነበረውን ወዳጅነትና ክብር አጉልቶ የሚያሳይ የታሪክ ማስረጃ ነው።

በኢትዮጵያና በአሜሪካ ያለውን ወዳጅነት የኢትዮጵያ ሕዝብ በከፍተኛ ደረጃ የሚመለከተውና የሚያየው ነው። ስለኢትዮጵያ ትክክለኛ ሁናቴ በበለጠ ለማየትና ለመገንዘብ ከውጭ ምሁራን በሚሠጡት አስተያየቶች በቂ ሳይሆኑ በተጨማሪም ባህሉን፥ ልምዱንና አስተሳሰቡን ከሚያውቁት ኢትዮጵያውያን ምሑራንም ጭምር ግንዛቤ ቢወስድ ጠንካራና ትክክለኛ ሁናቴ ላይ መድረስ መቻሉን ማሳሰብ እንወዳለን።

በቅርቡ በኢትዮጵያ ለሚቋቋመው የሽግግር መንግሥት የኢትዮጵያ ሕዝብ በከፍተኛ ደረጃ እንደ ዓይኑ ብሌን የሚመለከተውና የሚጠብቀው ጉዳይ ስለሆነ እውነተኛ፥ ብሔራዊና ዲሞክራሲያዊ የኢትዮጵያውያንን ክብርና ሞገስ፥ ልዕልናና ዕኩልነት በትክክል የሚገነዘብ መንግሥት አምጭ አካል ስለሆነ እጅግ ከፍተኛ አደራና ጥንቃቄ ይጠበቅበታል። የኢትዮጵያውያን ምኞት፥ ሕልም ሁሉ ዕውን የሚሆንበትን ዕውነተኛ ጠንካራና ሕዝባዊ መንግሥት እንዲመሠረት የአገር ሽማግሌች፥ የሃይማኖት መሪዎች፥ ምሁራን፥ በጠቅላላው የአገሪቱ ዜጐች በወንድማማችነት፥ በፍቅር እንዲከናወን የአባትነት አደራችንን በኃያሉ በእግዚአብሔር ስም እናቀርባለን።

የኤርትራ ሕዝብ በደረሰበት የአስተዳደር በደል ቁጣውን አሰምቷል፥ ስለዕውነት፥ ስለዕኩልነት ተጋድሏል። ከዚህ ባሻገር ረሀብ፥ ጦርነት፥ ቸነፈር ሌላም ሌላ ከኢትዮጵያዊነት ከቶ የሚለየው አይኖርም አንድነቱ ዘለዓለማዊ ነው። የታሪካችን ሥር ቢመዘዝ ተተብትቦ የሚገኘው ጥንት ባህር ምድር እየተባለ ሲጠራ በኖረው ባሕር ነጋሽ ባሰኘው በኤርትራ ምድርና አፈር ነው። በታሪክ፡ በባህል፥ በደምና በሥጋ የተዋሃድን ነን። ሕልውናችን እንደ አንድ ልብስ አብሮ የተሠራ ነው። የፈትሎች ውህደት ልብስ የሚያሰኘውን ያህል የኤርትራና የቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብም አንድነት እንዲሁ ነው።

የኢትዮጵያ ታሪክ እንደሚያስገነዝበን የኢትዮጵያ ጠ/ግዛቶች ራሳቸውን ችለው የሚኖሩና ለነሱም ገዢዎች እስከ ነገሥታት ድረስ ነበሯቸው። የእነዚህ ነገሥታት የበላይ ደግሞ "ንጉሠ ነገሥት" ነበሯቸው። ለዚህም ነው በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የሚለው ስም ሲያያዝ የመጣው። ይህም የሚያሳያው እያንዳንዱ የጠ/ግዛት ሕዝብ በባህሉና በልማዱ ይተዳደር እንደነበር እንገነዘባለን። በተለይም አሁን የተለያዩ ፓርቲዎች የተወለዱበትና ያደጉበት ወቅት በመሆኑ እውነተኛና ነፃ የሆነ ዲሞክራሲያዊ ምርጫ እየተካሄደ ሕዝቡን ራሱን በራሱ እንዲያስተዳድር ለብዙ ጊዜ የምንመኘውና የምንፈልገው ጊዜ በመምጣቱ ከፍተኛ ጥንቃቄና ብልሃት በተመሳበት አኳኋን እንዲፈፀም ከአደራ ጋር እናስገነዝባለን።

እኛም ባለንና በነበረን ታሪካችንና ባህላችን መሠረት በሕግ በተወሰነ የዘውድ መንግሥት የታሪክ ድባብ በመሆን ለማገልገል ዝግጁነታችንን እናረጋግጣለን።

በመጨረሻም ለኢትዮጵያ ጥንታዊ የዘውድ ሥርዓት ተቆርቋሪና ደጋፊ የሆኑ አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን፥ ዘውዱ በኢትዮጵያ ውስጥ ተመልሶ ተገቢ የሆነ ቦታውን እስኪያዝ ድረስ ተግቶ የሚሠራ፥ የኢትዮጵያን አንድነት፥ ታሪክ፥ ነፃነት፥ መብት፥ ክብርና ልዕልና ከፍ ለማድረግና ለማስጠበቅ አንዳንድ አሰባሳቢ እንዲሆን "ሞዓ አንበሳ" በሚል ሥያሜ ለአቋቋሙት አካል እኛ የበላይ ጠባቂ እንድንሆን ጠይቀውን ኃሳቡን በደስታ ተቀብለነዋል።

ስለዚህ ለኢትዮጵያ ታሪክ ልዕልና ክብር የምትመኙና የምታስቡ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ይኸው አሰባሳቢ አካል ባዘጋጀው በዓል ላይ እንድትገኙለት ማሳሰቢያችንን እናስተላልፋለን።

ለሁሉም ኃያሉ እግዚአብሔር ይርዳን።

ኢትዮጵያ ታበጽሕ ዕደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር።

ቀዳማዊ አምኃ ሥላሴ
ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ።

ሞዓ አንበሳ አዲስ አበባ ውስጥ
በቀ. ኃ. ሥ. ትያትር እንደገና
ሲመሠረት የነበረው ክብረ በዓል

ከገጽ ...6... የዞረ

በዘውድ ስም ተዋግተው ሕይወታቸው ላለፈው ጀግኖች ክብርና በመንቀሳቀስ ላይ ለሚገኘው ሠራዊት ተስፋ ሆነለት ወድቆ የነበረውን የጦር እንቅስቃሴ ለማደራጀትና በንጉሠ ነገሥቱ ስም የጦር ካቢኔ ለማቋቋም ወሰነ። በስደት ላይ የሚገኘውን የኢትዮጵያን የጦር አባሎች ለማደራጀትና ለማሳበሰብ፣ የሕዝቡንም መንፈስ ለመቀስቀስ፣ በስደት ላይ የሚገኘውን የዘውድ መንግሥት መሠረተ። ሕገ መንግሥቱን መሠረት በማድረግ ሕዝቡ በመረጠው ጠቅላይ ሚኒስትር እንዲተዳደር ወሰነ።

በሳውዲ አረቢያ ጥር 23 ቀን 1976 ዓም ባስተላለፈው የዘወድ ምክር ቤት ውሳኔ ንጉሠ ነገሥቱ የዘውድ ምክር ቤቱን ውሳኔ መጋቢት 29 ቀን 1980 ዓም ተቀብለው አፀደቁ። ባስተላለፉትም ውሴኔና ለሕዝባቸው የሰጡት ያዋጅ መግለጫ እንደሚከተለው ነበር።

"በታሪካችን ሲወርድ ሲዋረድ በመጣው ወራሴ መንግሥትነታችን ከገናናው አባታችን ከአፄ ኃይለ ሥላሴ ተረክበናል የዘውዱን ሥርዓት አፈጻጸም ሕዝባችን ነፃነቱን ካገኘ በኋላ በመካከሉ ተገኝተን፣ በሃይማኖታችን፣ በባህላችን የንግሥና ስርአታችንን እንፈጽማለን። ለሕዝባችን ክብርና ኃይል ማስተባበሪያ ይሆናል ተብሎ ምክር ቤታችን ያመነበትን የስም መጠሪያ ተቀብለን አጽድቀናል።

በሕገ መንግሥታችን በተወሰነው መሠረት ሕዝቡ በመረጠው ጠቅላይ ሚኒስትርና የፓርለማ ሸንጐ እንተዳደራለን ሲሉ ውሳኔ አስተላልፈዋል።"

"አፄ ኃይለ ሥላሴ ልዑል ዘርዓ ያዕቆብ አምኃ ሥላሴን ተጠባባቂ አልጋ ወራሽ በማለት ሸመዋቸው የነበረውን፣ አሁን የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት አልጋ ወራሽ ብለው ሸመዋቸዋል" ልዑል አስፋ ወሰን እሥራተ ካሣ፣ ክቡር አቶ ዘነበ ኃይሌ የጠቅላይ ምክር ቤቱ ፕሬዚዳንት የነበሩት፣ ልጅ አባተ ሙላት የዘውድ ምክር ቤት አባልና ስብሳቢ፣ ወይዝሮ ውለታ መካሻ የዘወድ ምክር ቤት ዋና ፀሐፊና አቶ አግሪ ጉግሣ የዘውድ ምክር ቤቱ አባል ባልታወቀ ምክንያት ተሻሩ።

ይቀጥላል.....

"MO-ANBESSA"

THE CONQUERING LION

የሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል መተዳደሪያ ደንብ

==============================

<u>የበላይ ጠባቂ</u>

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ አፄ አምኃ ሥላሴ ናቸው።

የሥራ አስካያጅ ቡድን አባላት፣

1. የሰብሳቢው አካል ተቀዳሚ ሊቀ መንበር
2. የሰብሳቢው አካል ሊቀ መንበር
3. የሰብሳቢው አካል ሊቀ መንበር
4. የሰብሳቢው አካል ም/ሊቀ መንበር
5. የሰብሳቢው አካል ም/ሊቀ መንበር
6. የሰብሳቢው አካል ዋና ጸሐፊ
7. የሰብሳቢው አካል ም/ዋና ጸሐፊ
8. የሰብሳቢው አካል ገንዘብ ያዥ
9. የሰብሳቢው አካል ም/ገንዘብ ያዥ

እንደአስፈላጊነቱ የሥራ አስኪያጅ ቡድን የተለያዩ ክፍሎችን ይመሠርታል።

አባልነት፣

ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ግለሰብ የሞዓ አንበሳን ዓላማ የሚደግፍ ሁሉ አባል መሆን ይችላል። እንዲሁም ዘውድ ከፖለቲካ ፓርቲዎች ሁሉ የበላይ ስለሆነና ሁሉንም ስለሚያቅፍ ከሞዓ አንበሳ ጋር አብሮ ለመሥራት ይችላል።

ተግባር፣

የሞዓ አንበሳ ተግባር በማንኛውም አመቺና ተስማሚ በሆነ መንገድ ሁሉ የሕዝብ ቅስቀሳ እያደረገ የዘውድን አቋም እንዲደግፍ የሚረዱትን ተግባራት ሁሉ ያከናውናል። ከነዚሁም መካከል፤

1. ዓላማውን የሚደግፉ ጽሑፍችንና ዜናዎችን ማሠራጨት
2. የሕዝብ ዕርዳታ አውታሮችን መዘርጋት
3. ሥራ አስፈፃሚ ቅርንጫፎችን በያሉበት ማቋቋም
4. አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ሁሉ የአባላት ምዝገባ ማቋቋም
   ማከናወን። ወዘተ.....

የሞዓ አንበሳ የሥራ አፈፃፀም፣

ሞዓ አንበሳ በኢትዮጵያ በሕግ የተወሰነ የዘውድ መንግሥት ተመልሶ እንዲቋቋም የሚንቀሳቀስ ሲሆን ከማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲና ድርጅቶች እንዲሁም ከማንኛውም ግለሰብ ጋር ለመሥራት የሚችል ሲሆን ይህም ማለት የሕዝቡ ሙሉ የዲሞክራሲ መብት የተከበረበት በሕግ የተወሰነ የዘውድ መንግሥት እንደ እንግሊዝና እንደ ጃፓን ዓይነት ነው። በውስጡ ግን ብዙ ፓርቲዎች የሚኖሩበትና በሕዝብ ምርጫ አገሪቱን የሚያስተዳድሩ አካላት የሚገኙበት ይሆናል።